# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☏ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

ቁጥር
Ref No. መኢ/ሰ/132/04
ቀን
Date 12/03/2004 ዓ.ም

ለሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር

<u>ዋሽንግተን ዲሲ</u>

ጉዳዩ፡ <u>የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ለሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር የሰጠውን ውክልና ስለማንሳቱ</u>

በሰሜን አሜሪካ የተቋቋመው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ድጋፍ ሰጭ ማኅበር እንደሌሎቹ ድጋፍ ሰጭ ማኅበራት ሁሉ አዲስ አበባ በሚገኘው በመኢአድ ህጋዊ ዕውቅና የተሰጠው መሆኑ ይታወሳል፡፡ በዚህ መሠረትም ድጋፍ ሰጭ ማኅበሩ መኢአድን በገንዘብ፣ በማቴሪያል፣ በሞራል፣ በምክር፣ በዲፕሎማሲያዊ ትግልና በመሳሰሉት በሚቻለው የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለብዙ ዓመታትም በዚሁ መንፈስ ተገቢውን ትብብርና ድጋፍ ማድረጋችሁ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ከ2003 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ አንስቶ የድጋፍ ማኅበሩ አመራር ከተቋቋመበት ዓላማ ፍፁም ተቃራኒ በሆነ መልኩ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይኸውም÷

1ኛ/ እራሱን ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በላይ በማድረግ የመኢአድን ህልውና ለከፍተኛ አደጋ ዳርጎት ከነበረው በአቶ ማሙሸት አማረ ከሚመራው አፍራሽ ቡድን ጎን በመቆም የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ስታደርጉ ቆይታችኋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየዞኑ ስልክ በመደወል የዞን አመራሮችን ከአፍራሽ ቡድኑ ጎን እንዲቆሙ ለማድረግ እና ፓርቲውን ለመከፋፈል ከፍተኛ ጥረት አድርጋችኋል፡፡ የመኢአድ ማዕከላዊ ምክር ቤት ሃምሌ 30/2003 ዓ.ም. ባካሄደው ጉባዔ የችግሩን ጥልቀት መርምሮ የአቶ ማሙሸት አማረ ቡድን እንዲባረር በከፍተኛ ድምፅ ማለትም በሰማኒያ ድጋፍና በሁለት ተቃውሞ በመወሰኑ የእናንተም ሆነ የሌሎች ፀረ-መኢአድ ኃይሎች ዕቅድ ሊመክን ችሏል፡፡ የተገለፀውን ተገቢ ያልሆነ ድርጊት መፈፀማችሁ አግባብ እንዳልሆነና በተለይም የእነ አቶ አስቻለው ከተማን ከፋፋይ እና አፍራሽ የሆነ እንቅስቃሴ እንድታስቆሙ እና ከፓርቲው ጎን እንድትቆሙ ላቀረብንላችሁ ጥሪ «የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ» ማለታችሁ ከልብ አሳዝኖናል፡፡

2ኛ/ በአሁን ወቅት ደግሞ ልክ እንደነ አቶ ማሙሸት አማረ የፓርቲውን ማህተም መያዣ በማድረግ እና ጠንካራ ጠንካራ አመራሮችን አስወግዶ በውህደት ሽፋን መኢአድን ለማጥፋት በወያኔ የአፈና መዋቅር ሙሉ ድጋፍ እየተደረገለት ከፍተኛ ደባ እየፈፀመ ከሚገኘው

እና ገና ከጅምሩ በመኢአድ የቁርጥ ቀን ልጆች ከተመታው ከአቶ ማህተመ በኩረና ከአቶ አሠፋ ሀብተወልድ ቡድን ጎን መቆማችሁ ሌላው አሳዛኝ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ አቋማችሁም በመኢአድ ስም ከፓርቲው ደጋፊዎች የተሰበሰበውን ገንዘብ በህጋዊ መንገድ በፓርቲው አካውንት ለመኢአድ መላክ ሲገባችሁ ህገ ወጥ ለሆኑት ግለሰቦች ወደ አዲስ አበባ በመላክ መኢአድን ለማፍረስ እንዲውል ማድረጋችሁን በተጨባጭ አረጋግጠናል፡፡ የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ዓለማ ደግፎ በስሙ የተቋቋመ ማኅበር ከዚያ ድርጅት በተቃራኒ የሚሄድ ከሆነ ድርጅቱ በስሙ እንዳይነገድበት ያለው ብቸኛ አማራጭ የሰጠውን ውክልና ማንሳት በመሆኑ የመኢአድ የስ/አ/ኮሚቴ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ከዛሬ ከህዳር 12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ውክልናችሁ የተነሳ መሆኑን እየገለጽን በመኢአድ ስም ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳታደርጉ ከአደራ ጋር እናሳስባለን፡፡

በሰሜን አሜሪካ የምትገኙ የመኢአድ ደጋፊዎች ግን ከዚህ በፊት ለሁለት አስርት ዓመታት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግ፣ ሀገራችሁንና ወገናችሁን ከአምባ ገነኖች የአገዛዝ ቀንበር ለማላቀቅ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ ከመሪ ድርጅታችሁ ከመኢአድ ጎን በመቆም በገንዘብ፣ በሞራልና በዲፕሎማሲያዊ ትግል ላደረጋችሁልን ከፍተኛ ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

**በሰሜን አሜሪካ የምትገኙ ከአመራር ውጭ ያላችሁ ደጋፊዎቻችን!**

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ዓላማና ፕሮግራም ዛሬም እንደ ትናንቱ ሳይሸራረፍና ለድርድር ሳይቀርብ እንደነበረ ያለ መሆኑን ተማምናችሁ አሁንም ከመኢአድ ጎን በመቆም ዝግጁነታችሁን በተግባር ጭምር እያሳያችሁን በመሆኑ ደስታችን የላቀ ነው፡፡ በቀጣይም እኛና እናንተ በመመካከር ተገቢው ጥናት ተደርጎ (በአውሮፓ እና በካናዳ እንዳሉ የድጋፍ ድርጅቶቻችን ሁሉ) በደግም ሆነ በክፉ ቀን የማይለየን መመከያ የሚሆን ጠንካራ የድጋፍ ማኅበር በሰሜን አሜሪካ እንደሚቋቋም እምነታችን የጸና ነው፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን በቡድንም ሆነ በተናጠል ሀገር ውስጥ ከሚገኘውና ፓርቲውን በህጋዊ መንገድ ከሚወክለው የመኢአድ አመራር ጋር በመነጋገር የተለመደውን ድጋፋችሁን ታደርጉልን ዘንድ በትግሉ በተሰው ወገኖቻችን ስም የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋንል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

ኃይሉ ሻዉል ግዛዉ (ኢ/ር)
የመኢአድ ፕሬዝዳንት
Hailu Shawel Gezaw
AEUP President (Eng)

ግልባጭ÷

- ለሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር አባላት በሙሉ

<u>በያላችሁበት</u>

<u>እንዲያውቁት</u>

- በካናዳ፣ በአውሮፓ፣ በአውስትራሊያ እና በደቡብ አፍሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጪ ማህበራት በያላችሁበት